# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

## የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ የ9ወር ዕቅድ

ጥቅምት / 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ ____ 2

1. የሁኔታዎች ትንታኔ ____ 3

1.1. ውስጣዊ ዳሰሳ....3

1.1.1. ተቋማዊ አደረጃጀት....3

1.1.2. የተቋሙ የሰው ሀይል....4

1.1.3. መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ....4

1.1.4. በአፈጻጸም የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች....4

1.2. ውጫዊ ዳሰሳ....5

1.2.1. መልካም አጋጣሚዎች....5

1.2.2. ስጋቶች....6

1.3. የባለስልጣን መ/ቤቱ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች....6

1.4. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች.... 7

1.5. የዕቅዱ የትኩረት መስኮችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች.... 7

2. የባለስልጣን መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ ግቦችና ክብደት....9

2.1. የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ የ9 ወራት ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት.... 9

2.2. የትግበራ፣ የክትትልና ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት....12

3. የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ የ9 ወራት ዕቅድ የሚከናወኑ ዋና ዋና ግቦች በቁልፍ ውጤት አመልካቾች....14

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ሀገር ሆና ለማየት የኢኮኖሚውን ዘርፍ በፍጥነት ከማሳደግ ጎን ለጎን የአካባቢ ጥበቃ ገዳዮችን በልዩ ትኩረት በመስራት ዜጎች በንጹህ አካባቢ የመኖር መብት እንዲረጋገጥና የዓላማችን ተግዳሮት የሆነው የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋምና የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ በታቀደውና በአለምዓቀፍ ስምምነት መሠረት በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡
የዘርፉ የ5 ዓመትና የ10 ዓመት ልማት ዕቅድ ግቦችን ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር ተቀናጅተው እንዲተገበሩ መመሪያዎችን በማዘጋጀት፣ የቴክኖሎጂ ፍላጎትና የፋይናንስ ምንጮችን በመለየትና ድጋፍ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እንዲዘጋጁ በማድረግ የተገኘውን ሀብት በየደረጃው ለስትራቴጂዉ ትግበራ ዉጤታማነት አጋዥ በሚሆን አግባብ ስራ ላይ እንዲውል የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

ሆኖም መስከረም 24/2014 ዓ.ም በተደረገው አዲስ የመንግሥት ምሥረታ እና የአስፈፃሚ፣ አካላት አደረጃጀት መሠረት አካባቢ ደን አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የነበረው በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በመተካቱ እንዲሁም የደን ዘርፍ የብዝሀ ህይወት እና የዱር እንስሳት ጥበቃ ተጠሪነታቸው ወደ ሌሎች አስፈፃሚ መ/ቤቶች ተጠሪ እንዲሆኑ በመደረጋቸው ይህን እቅድ መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
በዚሁ መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የ2014 በጀት አመት የልማት ዕቅድ ተከልሶ ሲዘጋጅ የዘርፉን ያለፉትን ዓመታት አፈጻጸም በመገምገም ለቀጣይ ዓመት የሚደረስባቸዉን ግቦች ከሀገራዊ የልማት እድገት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ከዘላቂ የልማት ግቦች፣ ከአፍሪካ አጀንዳ 2063፣ ሀገራችን የፈረመቻቸዉን አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች የትግበራ ደረጃ እንዲሁም ከዘርፉ አለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰርና በማጣጣም የተዘጋጀ ነው፡፡ በዋናነትም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣

አስቻይ የፖሊሲ ማዕቀፎችና የማስፈፀሚያ የፋይናንስ ዕቅድ እንዲሁም የዕቅድ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ስርዓትን በማመላከት የተዘጋጀ እቅድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት ደንብ ገና ያልተዘጋጀና ያልፀደቀ በመሆኑ ወደፊት የሚስተካከሉ ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## 1. የሁኔታዎች ትንታኔ

የዘርፉን ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች በመዳሰስ ያለውን በጥንካሬና በእጥረት የታዩ ጉዳዮች እንዲሁም መልካም አጋጣሚና ስጋት በመለየት መልካም አጋጣሚዎች እና ጥንካሬዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ በግብዓትነት እንዲውል ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በእጥረት የታዩ ጉዳዮች እና ስጋቶች ለዕቅዱ መሳካት አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖራቸው ቀድሞ በመለየት መፍትሄ መፈለግ አስፈላጊ በመሆኑ በሁኔታዎች ዳሰሳ ስትራቴጂያዊ የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ውስጣዊ እና ውጫዊ ዳሰሳ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.1. ውስጣዊ ዳሰሳ

በ2013 በጀት ዓመት በአፈፃፀም ወቅት ከተቋማዊ አደረጃጀት፣ ከሰው ሃይል፣ ከመሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ እንዲሁም ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር ውስጣዊ ዳሰሳ ቀጥሎ ባለው መልኩ ተዘርዝሯል፡፡

#### 1.1.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

የአካባቢ፣ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በሦስት አላማ አስፈጻሚ ዘርፎች፣ የማኔጅመንት ድጋፍ ሰጪ 10 ዳይሬክቶሬቶች እና በሥሩ ሦስት ተጠሪ ተቋማት፣ አስር ጀነራል ዳይሬክተሬቶች፣ 37 ዳይሬክቶሬሮች እንዲኖሩት ሆኖ ተደራጅቶ ሲሰራ የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በአዲሱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተብሎ መሰየሙ ቢታወቅም ደንቡና ተቋማዊ አደረጃጀቱ ባለመጠናቀቁ በቀጣይ የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈፀም የሚያስችል አደረጃጀቶችን ለመፍጠር፤ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ተግባራት ታቅደዋል፡፡

### 1.1.2. የተቋሙ የሰው ሀይል

ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በአጠቃላይ ወንድ 199 ሴት 129 በድምሩ 328 የሰው ኃይል ያለው ሲሆን ዝርዝሩ በቀጣይ ሠንጠረዥ ተቀምጧል፡፡

| ተ.ቁ | የተቋሙ ዘርፎች | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መደበኛ ሰራተኞች | 172 | 127 | 299 |
| 1.1 | የአከባቢ ዘርፍ | 71 | 16 | 87 |
| 1.3 | የአየር ንብረትና ብዝሀሕይወት ዘርፍ | 28 | 10 | 38 |
| 1.4 | የድጋፍ ሰጪ ዘርፍ | 71 | 100 | 171 |
| 1.5 | ተሻሚዎች | 2 | 1 | 3 |
| 2 | የፕሮጀክት ሰራተኞች | 27 | 2 | 29 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **199** | **129** | **328** |

### 1.1.3. መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ

ባለስልጣን መ/ቤቱ የራሱ የሆነ ቢሮ ባይኖረውም ግንባታ ለማካሄድ ጥያቄ በማቅረብ ሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለቢሮ አገልግሎት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት (የኢንተርኔት፣ የወረዳ ኔት፣ የገመድና ገመድ አልባ ስልኮች፣ የ4ጂ ኢንተርኔት አገልግሎት፣ የተለያዩ የኢኮቴ ቁሳቁሶች መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸትና ለመተንተን የሚያስችሉ የኢንፎርሜሽን ሲስተሞች) የተደራጀ ነው፡፡

### 1.1.4. በአፈጻጸም የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

#### 1.1.4.1. ጠንካራ ጎኖች

- የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማዘጋጀት ተቋማዊ አቅም መገንባቱ፣
- በዘርፉ ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ ትስስርና አጋርነት እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የፋይናንስና ንብረት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ መወሰዱ፣
- የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማጎልበት በአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲ፣ ህጎችና ስትራቴጂዎች ላይ በተለያዩ ስልቶች የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማጎልበት መቻሉ
- ለዘርፉ ልማት ጉልህ ሚና የሚኖራቸዉ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መዘጋጀታቸው፣
- የዘርፉን ሥራ ለማሳለጥ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከልማት አጋሮችና ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋራ የግንኙነት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱ፣

- በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ የሀገራችን ፍላጎትና አቋም ማንፀባረቅ መቻሉ፣
- በየደረጃው ላሉ አመራሮችና ባለሞያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መሰጠቱ፣
- የመጤና ወራሪ ዝርያዎች ስትራቴጅ /National IAS Strategy/ መዘጋጀቱ፣

1.1.4.2. **ደካማ ጎኖች**

- በዘርፉ ከፌዴራል እስከ ታችኛው የአስተዳደር የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ህጎችና ደንቦች ብሎም አሰራሮች እንዲሁም ስርዓቶችን ለመተግበር የሚያስችል አደረጃጀት የተናበበ ያለመሆኑ፣

- ከሚመለከታቸው የፌደራልና ክልልና ከተማ አስተዳደር የክትትል፣ ግምገማና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የተጠናከረና ወቅታዊ አለመሆኑ፣
- የራሱ የሆነ ጽ/ቤት (ቢሮ) ህንፃ ያለመኖር ከዚህ ጋር ተያይዞ የራሱ የመሠረተ ልማት ጉዳዮችን ለማሟላት አስቸጋሪ መሆኑ፣
- የማዕቀፍ ግዥ መዘግየት ሥራ ላይ ጫና መፍጠሩ፣

## 1.2. ውጫዊ ዳሰሳ

ሀገራችንን በ2025 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ጥረት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ሀገራዊ የ10 ዓመት የልማት እቅድ ምሰሶዎች ውስጥ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት መገንባት አንዱ ሆኖ ተካቷል፡፡ የዘርፉን የማስፈጸምና የመፈፀም አቅም ለመገንባት የተለዩ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 1.2.1. መልካም አጋጣሚዎች

- መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆንና የተጠናከረ ድጋፍ እያደረገ የሚገኝ መሆኑ፣
- በመንግስት የሚሰሩ የአረንጓዴ ልማት ዕቅድ የሚያሳኩ ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ሜጋ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚመጣውን ተፅዕኖ ምላሽ ለመስጠት የህበረተሰባችን ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፣
- በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚደረጉ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ከፍተኛ ሀገራዊ አስተዋፅኦ ያላቸው መሆኑ፣
- በዘርፉ ሊያሠሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች መኖራቸው፣

- ለዘርፉ ልማት ስራዎች የሚደረጉ አለም አቀፍ ድጋፎች እየጨመሩ መምጣታቸዉ

1.2.2. ስጋቶች

- የክልሎችና የዘርፍ መ/ቤቶች ተቋማዊ አደረጃጀት ወጥነትና ተናባቢነት የሚጎለው ከመሆኑም በላይ የተወጠኑ ሀገራዊ ግቦችን በአስተማማኝ መልኩ ለመፈጸም የሚያስችል የተሟላ ቁመና ያለው የዘርፉ የተናበበ ተቋማዊ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖሩ፣
- ጥራቱንና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት እና መረጃ ከዘርፎችና ከክልሎች አለመላኩ፤
- ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከልውጠ ሕያው ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቤተ ሙከራ ለማስጀመር የህግ ክፍተት መኖሩ፣
- ያልተረጋጋና ተደጋጋሚ የሆነ የተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት መለዋወጥ ፣
- በአለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽን ምክንያት በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውስ በመፍጠሩ እንደ ዘርፍ የታቀዱ እቅዶችን ለመፈጸም ተግዳሮት መሆኑ፣
- ስለአካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ በተለያዩ አካላት ያለው ግንዛቤ ውስንነት፣
- አደገኛ ኬሚካሎችና ቆሻሻዎች ለማስወገድ ለማከማቸትና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሀገራዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና የቴክኒክ እውቀት የአቅም ውስንነት መኖሩ፣
- የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መጨመር፣ ብዝሀ ሕይወት መመናመን፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣

## 1.3. የባለስልጣን መ/ቤቱ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች

### ራዕይ

ዘላቂ የአከባቢ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በመተግበር ዜጎች በንፁህ አካባቢ የመኖር መብትን በማረጋገጥ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ መደላድል በመፍጠር ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ሀገር ሆና ማየት፣

### ተልዕኮ

አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስችሉ የአካባቢ አያያዝና አጠቃቀም ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሣ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሥርዓትን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነቱን ማረጋገጥ፣ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ትምህርትና ግንዛቤን ማስፋፋት ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ትግበራን በዘርፍ መ/ቤቶችና በክልሎች በማስተባበር ፣

የተግባሪዎችን አቅም መገንባት፣ ዓለም አቀፋዊ የአካባቢና የአየር ንብረት ድርድሮችንና ስምምነቶች ትግበራን የመምራትና የመከታተል እና ወቅታዊ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባን ማዘጋጀት ነው፡፡

**ዕሴቶች**

- ታታሪነት፣ ቅንነት፣ ግልፀኝነት
- የዜጎችን እርካታ ማረጋገጥ
- ከባለድርሻዎች ጋር በህብረት መስራት
- ለበጎ ለውጥ ዝግጁ መሆን
- የህግ የበላይነትን ማክበር
- የተልእኮ ቁርጠኝነት
- ታዓማኝነት

## 1.4. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

የባለስልጣን መ/ቤት የተከለሰ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ የተዘጋጀው ቀጥለው የተዘረዘሩትን መነሻ ሀሳቦች ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

- ሀገራዊ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣
- የኮሚሽን መ/ቤቱ የ10 ዓመት (2013-2022) እና የ5 ዓመት (2013-2017) ስትራቴጂክ ዕቅድ፣
- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ የግብር እና አርብቶ አደርና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ግብረ-መልስ
- የኮሚሽን መ/ቤቱ የ2013 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ
- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራተጂና የክትትልና ግምገማ ስርዓት
- በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተከለሰ የአየር ንብት ለውጥ ዕቅድ (Updated NDC)
- የኦዲት ግኝት (የፋይናንስና ክዋኔ ኦዲት) ምልከታ
- የዘላቂ ልማት ግቦችና፣ የአፍሪካ አጀንዳ 2063 እና አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች

## 1.5. የዕቅዱ የትኩረት መስኮች እና መሰረታዊ አቅጣጫዎች

### 1.5.1. የዕቅዱ የትኩረት መስኮች

የተቋሙን ተልዕኮ ከማሳካት ብሎም ራዕዩ ዕውን ከማድረግ አኳያ ተቋሙ በአዋጅ የተሠጠውን ስልጣንና ተግባር፣ ያሉትን እሴቶች እና የባለድርሻ አካላት እንዲሁም በዘርፉ ያሉትን ጥንካሬዎች እና ድክመቶች እንዲሁም ሊኖሩ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን በመተንተን በየደረጃው የሚገኘው አስፈፃሚዎች እና ፈፃሚዎች የጋራ አቅጣጫ ይዘው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ተለይተዋል:: በዚህም መሰረት የተቋሙ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ሆነው የተመረጡት የሚከተሉት ናቸው፡

| ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዊ ውጤቶች |
|---|---|
| የአካባቢ ህግ ተከባሪነትን ማረጋገጥ፣ | • የተረጋገጠ የአካባቢ ደህንነት |
| የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽኖ ቅድመ ጥናት መፈጸሙን ማረጋገጥ | • የተሰጠ የይሁንታ ፍቃድ |
| የአካባቢ ጥበቃ ስራ የሙያ ብቃት ማረጋገጥ | • የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ |
| የደህነተ ህይወት ማረጋገጥ | • የተረጋገጠ የደህንነት ህይወት |
| የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽን (ማጣጣምና ማስተስረይን) ማስተባበር፣ | • ውጤታማ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ምላሽ |
| የአካባቢ ጉዳዮች ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት | • የጐለበተ የማህበረ ሰብ አቅም/ግንዛቤ |
| ስርዓተ ምህዳር ጥበቃን ማረጋገጠ | • የተጠበቀ ስነምህዳር |

### 1.5.2. መሰረታዊ አቅጣጫዎች

- ቀጣይነት ያለው የአሰራር ጥራትና ውጤታማነትን በባለስልጣን መ/ቤቱ ማጠናከር፣
- የተገልጋዮችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የተቋሙን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በመገንባት የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ማጐልበት፣
- የዘርፉን የሰው ሃብት ልማትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን ማፋጠንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ፣
- የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣
- የተፈጥሮ ሀብት እና አከባቢ ጥበቃን ተግባራትን ማጠናከር፣

- ግልፀኝነት፣ ቅንነትና ታዓማኝነትን ማጎልበት

## 2. የባለስልጣን መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ ግቦችና ክብደት

| ዕይታ | ስትራቴጂክ ግቦች | ጠቅላላ ክብደብ በ% |
|---|---|---|
| ተገልጋይ (20%) | ግብ 1 ፡- የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | 20 |
| ፋይናንስ (15%) | ግብ 2 ፡- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | 10 |
| | ግብ 3 ፡- የሀብት ግኝትን ማሳደግ | 5 |
| የውስጥ አሠራር(40%) | ግብ 4 ፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል | 15 |
| | ግብ 5፡- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት | 15 |
| | ግብ 6፡- በአካባቢ ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ | 5 |
| | ግብ 7፡- የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎና ማሳደግ፣ | 5 |
| መማርና እድገት (25%) | ግብ 8 ፡- የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ማሳደግ፣ | 10 |
| | ግብ 9፡- የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣ | 15 |

### 2.1. የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ የ9 ወራት ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት

በዘርፉ ዘጠኝ ግቦች ተቀርጾ በተስማሚ የአፈጻጸም አመልካቾች፣ መለኪያዎችና የበጀት አመቱ ኢላማዎች የተዋቀረ ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**ግብ 1 ፡- የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታ ከ 83 % ወደ 88% ማሳደግ
- በአገልግሎት አሰጣጥ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመከታተል 100% ምላሽ መስጠት

**ግብ 2 ፡- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- በፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ መሰረት 100 % በጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ
- በኦዲት ግኝት ላይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃ በመውሰድ 100 % ማከናወን
- የሀብት ብክነትን 100 % መቀነስ

**ግብ 3 ፡- የሀብት ግኝትን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች 50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሰበሰብ ማድረግ

**ግብ 4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- ተጨማሪ በአመቱ 39.5 ሚ.ሜ.ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድ እኩሌታ (MtCO2eq.) የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነሱን በማረጋገጥ በአጠቃላይ በአመቱ 144.99 MtCO2eq የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነስ፣
- ሦስተኛ ሀገራዊ National communication Report እና Biennial Update Report አንድ ሰነድ ማዘጋጀት
- የ2012 እና የ2013 ዓ.ም ሀገራዊ ዓመታዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትና ቅነሳ ዘገባ አንድ ሰነድ ማዘጋጀት
- የሙቀት አማቂ ጋዞች ቆጠራ ዘገባ 2 ሰነዶች ማዘጋጀት
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን 100% ሜንስትሪም ያደረጉ 12 ተቋማት ላይ 4 ጊዜ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ መስጠት፤
- 8 ኢንዱስትሪዎች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአመራረት ሥርዓት እንዲያቋቁሙ መደረጉን ክትትል ማድረግ
- 30 ከተማ አካባቢዎች በአረንጓዴ መሰረተ ልማት የተሸፈኑ መሆኑን ክትትል ማድረግ
- በአካባቢ ብክለት ችግር አጋጥሟቸው ህክምና ያገኙ ግለሰቦች ድርሻ 0.3 በመቶ ማድረሱን ክትትል ማድረግ
- በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅዱ ላይ የተለዩትን 18 የማጣጣሚያ ዘዴዎች አካተው ተግባራዊ ያደረጉ ፕሮጀክቶች ድርሻ 55% ማድረስ
- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ የሚረዱ 2 ሰነዶችን ማዘጋጀት
  - በግብርናና ደን ሴክተር መ/ቤቶች በሀገራዊ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅድ ለመስጠት የሚያግዝ የአቅም ግንባታ ዳሰሳ 1 የጥናት ሰነዶች ማዘጋጀት፤
  - ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን መከለስ

- ለአረንጓዴ ልማት ትግበራ ውጤታማነት አጋዥ የሚሆኑ 21 የአረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን እንዲተገበሩ ማድረግ፣
- የአየር ንብረት ለውጥ እና የአከባቢ ድርድር ውጤታማነትን 100 % ማከናወን
- በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች እና ፎረሞች ላይ የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ 18 ሰነዶችን ማዘጋጀት
- በ18 የአካባቢ ስምምነቶች የድርድር መድረኮች ተሳትፎ ማድረግ
- ከልማት አጋር አካላት ጋር የአጋርነት መፍጠሪያና ማጠናከሪያ 50 የሁለትዮሽና የባለብዙ የውይይት መድረኮች ማዘጋጀትና መሳተፍ

**ግብ 5፡- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- 70 ከተሞች የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ ዕቅድ አዘገጅተው እንዲተገብሩ ድጋፍ ማድረግ
- የኦዞን አሳሽ ኬሚካሎችን ቁጥጥር በማካሄድ የ HCFC ቅነሳን 47.5 % ማድረስ
- የአከባቢ ጥበቃ ህጎች ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማትን ድርሻ በ20% ማሳደግ
- 4 ሚሊዩን የህብረተሰብ አካለት ግንዛቤ መስጠት
- 750 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሊከስት የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን መቀነስ የሚያስችል የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በማድረግ ርምጃ መወሰዳቸውን ማረጋገጥ፤
- በሀገሪቱ ስታንዳርድ መሰረት 14412 የማምረቻ፣ የልማት ፕሮጀክቶች እና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የአካባቢ ህግ አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፤
- የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ በሰው እና በአካባቢ ላይ ጉዳት አለማስከተሉን ክትትል በማድረግ የተቀናጀ የአደገኛ ቆሻሻ እና የኬሚካል አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው መተግበራቸውን 40 ተቋማት ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ
- ለ5863 ፕሮጀክቶች የአካባቢ አያያዝ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ
- ለ2696 የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ አቤቶታና ጥቆማ በመቀበል ማጣራትና ምላሽ መስጠት
- ለ7300 የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ እንዲያገኙና እንዲተገብሩ ማድረግ
- 1520 ነባር ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እዲያቀርቡና እንዲያጸድቁ ማድረግ፣
- የይሁንታ ፈቃድ ለተሰጣቸው 5117 ፕሮጀክቶች እና ፓርኮች የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት በማድረግ ክፍተት ባላቸው ፕሮጀክቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ

- በአካባቢ ዘርፊ ለ1150 የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት መስጠት
- አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ 400 ቶን አደገኛ ቆሻሻ  ማስወገድ
- በ4 በተጎዱ ሥርዓተ ምህዳሮች ላይ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ፋክት ሺት ዘገባ ማዘጋጀት
- 8 የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ዘገባ ማዘጋጀት
- 6 የአካባቢ ህግና ስርዓቶችን ማዘጋጀት

**ግብ.6 - በአካባቢ  ሀብት  ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- የመጤ ወራሪ አረም ሽፋን መጠን በ160000ሄ/ር እዲቀንስ ማድረግ
- አንድ የደህንነተ ሕይወት ሥርዓት በመዘርጋት ሊድርስ የሚችለውን ጠንቅ መቀነስ
- የ2 ስርዓተ ምህዳር ግልጋሎት ዋጋ ትመና ቅድመ ጥናት ማድረግ

**ግብ 7፡- የመረጃና ቴክኖሌጂ አቅርቦትና ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም እና የልውውጥ ስርዓት በ30 % ማሳደግ
- 4 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ስራ ላይ ማዋል
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ተጠቃሚነትን 60 % ማድረስ
- ተዘጋጅቶ የተሰራጩ አገራዊ 6 ዘገባ/ሪፖርት ማዘጋጀት

**ግብ 8 ፡- የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎ ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- በዘርፎችና በክልሎች የሴቶች ተሳትፎ ስለመረጋገጡ ክትትል ማድረግ
- በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት የበቁና ያደጉ ሴቶች ተሳትፎ ማሳደግ

**ግብ 9፡- የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮች**

- የአጭር ጊዜ ስልጠና  ወንድ 1400 ሴት 700 በድምሩ 2100 ሰልጣኞች ስልጠና መስጠት
- የረጅም ጊዜ ስልጠና በመጀመሪያ ድግሪ 2 በሁለተኛ ድግሪ 6 በሦስተኛ ድግሪ 4 በድምሩ 12 ሰልጣኞች ስልጠና መስጠት
- 4 ምርጥ ተሞክሮ መቀመር

## 2.2. የትግበራ፣ የክትትል፣ግምገማና ግብረ-መልስ ስርአት

### 2.2.1. የእቅዱ አተገባበር

ይህ ዕቅድ የባለስልጣን መ/ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት በጥቅሉ የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ዘርፍ በስሩ በያዘው ዝርዝር አመታዊ እቅድ መሰረት ስራዎችን ያከናውናል፡፡ ሁሉም ጀነራል ዳይሬክቶሬቶችና ዳይሬክቶሬቶች በስራቸው ላሉ ፈጻሚ ንኡስ የስራ ክፍሎችና ግለሰቦች ድረስ ተፈራርሞ ማውረድና በዚሁም መሰረት የእለት ተዕለት ተግባሩን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ለዕቅዱም ተግባራዊነት በበላይ አመራሮች ፣ጀነራል ዳይሬክቶሬቶች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት መካከል የጠበቀ ግንኙነት መኖርና ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

### 2.2.2. የክትትልና ድጋፍ ስርአት

የታቀደው ዕቅድ ትግበራ ወቅት በባለስልጣን መ/ቤቱ የክትትልና ድጋፍ ስርአት ተዘርግቶ በተለያየ ደረጃ ያሉ ፈጻሚዎችና ሃላፊዎች በሚያከናውኑት የጋራ መድረክ፣ በሚቀርብ መደበኛ ሪፖርት በመስክ ላይ በሚደረግ ምልከታ መሰረት አፈጻጸሙን (የእቅድ አተገባበር) በመከታተል የሚያጋጥሙ ችግሮች ከስር ከስር በመፍታትና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የታቀደውን ሙሉ በሙሉ ለማሳከት ርብርብ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት የክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ ሂደቱ በተለያ ደረጃዎችና አካላት በአሳታፊ መልኩ እንደሚመለከተው ይከናወናል፡፡

- **በግለሰብ ደረጃ፡-** በክፍል ደረጃ የዕለት ወይም የሳምንት አፈፃጸማቸውን ያጋጠማቸውን ችግሮች ገምግመው በየሳምንቱ ለቅርብ ሃላፊዎች ሪፖርት ያደርጋሉ፤
- **በዳይሬክተር ደረጃ፡-** በየሳንቱ በስሩ ላሉ ቡድኖች (አደረጃጀቶች) እና ግለሰቦች ስለ ሳምንቱ አፈጻጸም ግብረ መልስ ይሰጣል፤ቀጣይ የሳምንት እቅዳቸውን ያጸድቃሉ፡፡ ከዚያም የዳይሬክቶሬቱን አጠቃላይ ሂደት ገምግሞ በየ15 ቀኑ ለቅርብ የስራ ሃላፊዎች ሪፖርት ያደርጋል፤
- **በጀነራል ዳይሬክተር ደረጃ፡-** በስሩ ላሉ ዳይሬክቶሬቶች በየወሩ የቀረበለትን ሪፖርት መሰረት አድርጎ በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ወይም በጽሁፍ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡ ከዚያም የጀነራል ዳይሬክቶሬቱን አጠቃላይ ሂደት ገምግሞ በየወሩ ለሚመለከተው ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፡፡
- **በፕሮግራም (ትኩረት መስክ) በዘርፍ ደረጃ፡-** የትኩረት መስክ ባለቤቶች (የዘርፍ ኃላፊዎች) ከጀነራል ዳይሬክቶሬቶችና ዳይሬክተሮች ጋር በየወሩ የጋራ መድረክ

በማካሄድ ስራዎችን ይገመግማሉ፤ ለጀነራል ዳይሬክቶሬቶችና ለዳይሪክቶሬቶች ግብረ መልስ ይሰጣሉ፤በትኩረት መስክ ደረጃ አፈጻጸሞችና ያጋጠሙ ችግሮች ለበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

- **በኮርፖሬት ደረጃ፡-** በየትኩረት መስኮች የቀረቡት የክትትል ሪፖርቶችና ከሌሎች ምንጮች የተገኙ መረጃዎች መሰረት በማድረግ በከፍተኛ አመራሩ ደረጃ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ተወያይተው ለችግሮች አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፤ ሰለአጠቃላይ ሂደት ግብረ- መልስ ያገኛሉ፡፡

የክትትልና ድጋፍ ተግባር በየጊዜው የሚሰጡትን ግብረ መልሶች ማዕከል በማድረግ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚከናወን ሲሆን የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር ከሌሎች የስራ አመራር ጋር በመተባበር በባለስልጣን ውስጥ ያሉትን የስራ ክፍሎች የዕቅድ አፈጻጸም የመከታተል፣የመደገፍ ሃላፊነት አለበት፡፡

### 2.2.3. የማጠቃለያ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ

የስራ ክፍሎችና የተቋሙ መደበኛ የአፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርበው በየሩብ ዓመቱ ሲሆን በተቋሙ ደረጃ የታቀዱ የስራ እንቅስቃሴዎች የሚለኩት የመስክ ጉብኝት (ሱፐርቪዥንና) በባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚገኙ የተለያዩ የስራ ክፍሎች ከሚገኝ መደበኛ ሪፖርት ነው፡፡ ለፈጻሚ የስራ ክፍሎች ደግሞ ሪፖርት በዋናነት በየጊዜው ከተደረጉት የክትትል ሪፖርቶችና አፈጻጸም ሪከርዶች የሚመነጭ ሲሆን የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክተር የተቋሙን የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ አመቱ አዘጋጅቶ በማኔጅመንት ካውንስል በማጸደቅ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

## 3. የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ የ9 ወራት ዕቅድ የሚከናወኑ ዋና ዋና ግቦች በቁልፍ ውጤት አመልካቾች

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | **ግብ 1 ፡- የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 83 | 88 | 88 | | | 88 | |
| | በአገልግሎት አሰጣጥ ለሚነሱ ቅሬታዎች የተሰጠ ምላሽ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | | | 100 | |
| | **ግብ 2 ፡- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | በኦዲት ግኝት ላይ የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 75 | 100 | | |
| | የቀነሰ የሀብት ብክነት | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | **ግብ 3 ፡- የሀብት ግኝትን ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | ለማጣጣሚያና ማስተሰሪያ ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | 0.453 | 50 | 50 | 15 | 25 | 10 | |
| | **ግብ 4 ፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል** | | | | | | | | |
| | ሀገራዊ የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ሜ/ቶን | 104.99 | 144.49 | 144.49 | | | 144.49 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የተዘጋጀ የ2012 እና የ2013 ዓ.ም ሀገራዊ ዓመታዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትና ቅነሳ ዘገባ በሰነድ | | ቁጥር | 1 | 1 | **1** | | | 1 | |
| | National communication Report እና Biennial Update Report ሰነድ | | በሰነድ ቁጥር | | 1 | 1 | | | 1 | |
| | የሙቀት አማቂ ጋዞች ቆጠራ ዘገባ ሰነድ | | በሰነድ ቁጥር | - | 2 | 2 | 2 | | | |
| | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ | ሜይንስትሪሚንግ ያደረጉ ተቋማት | በመቶኛ | 100 | 100 | **100** | 100 | 100 | 100 | |
| | | ለዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጠ ግብረ መልስ | በቁጥር | 4 | 4 | **3** | 1 | 1 | 1 | |
| | | ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ ግብረ መልስ | በቁጥር | 1 | 4 | **3** | 1 | 1 | 1 | |
| | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአመራረት ሥርዓት ያቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | | በቁጥር | 7 | 8 | 8 | | | 8 | |
| | በአረንጓዴ መሰረተ ልማት የተሸፈኑ ከተማ አካባቢዎች ብዛት | | በቁጥር | 8 | 30 | 30 | | | 30 | |
| | በአካባቢ ብክለት ችግር አጋጥሟቸው ህክምና ያገኙ ግለሰቦች ድርሻ | | በመቶኛ | | 0.3 | 0.3 | | | 0.3 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅዱ ላይ የተለዩትን 18 የማጣጣሚያ ዘደዎች አካተዊ ተግባራዊ ያደረጉ ፕሮጀክቶች ድርሻ | በመቶኛ | **50** | **55** | 55 | | | 55 | |
| | ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ የሚረዱ የተዘጋጁ ሰነዶች | ቁጥር | 4 | 2 | 2 | 1 | | 1 | |
| | የሙቀት አማቂ ጋዞች ቆጠራ ዘገባ ሰነድ | በሰነድ ቁጥር | - | 2 | 2 | 2 | | | |
| | ተግባራዊ የተደረገ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ | በቁጥር | 23 | 21 | 21 | | | 21 | |
| | የአየር ንብረት ለውጥ እና የአካባቢ ድርድር ውጤታማነት | በመቶኛ | 92.5 | 100 | 100 | | | 100 | |
| | የሀገራችን ፍላጎትና አቋም የሚያሳዩ የተዘጋጁ ሰነዶች | ቁጥር | 27 | 18 | **15** | 10 | 2 | 3 | |
| | ተሳትፎ የተደረገባቸው የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር መድረኮች | ቁጥር | 16 | 18 | **15** | 10 | 2 | 3 | |
| | የተዘጋጁና ተሳትፎ የተደረገባቸው የአጋርነት መፍጠሪያና ማጠናከሪያ የሁለትዮሽና የባለብዙ የውይይት መድረኮች | ቁጥር | 50 | 50 | **45** | 20 | 15 | 5 | |
| | **ግብ 5 ፡- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት** | | | | | | | | |
| | የተዘጋጁ ስርአቶች | በቁጥር | 6 | 6 | **5** | | | 5 | |
| | **የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ፖሊሲ ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች ድርሻ** | **በቁጥር** | 20 | 70 | | | | 20 | |
| | የHCFC አጠቃቀም አዝማሚያ ቅነሳ ዕድገት | **በመቶኛ** | 41.25 | 47.5 | 47.5 | | | 47.5 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የአከባቢ ጥበቃ ህጎች ተግባረዊ ያደረጉ ተቋማት ድርሻ | **በመቶኛ** | 10 | 20 | 20 | | | 20 | |
| | የአደጋ ተጋላጭነት መቀነስ አዘማሚያ ምጣኔ | በመቶኛ | 65 | 68 | 68 | | | 68 | |
| | ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ  አካለት በሚሊዮን ቁጥር | በሚሊየን | 2.1 | 4 | **3.5** | 1 | 1 | 1.5 | |
| | የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ አዘገጅተው እየተገበሩ ያሉ ከተሞች | ክትትል ና ድጋፍ የተደረገ | 643 | 750 | **685** | 200 | 285 | 200 | |
| | በአገሪቱ  ስታንዳርድ መሰረት ቁጥጥር የተደረገባቸው ተቋማትና ፕሮጀክቶች ብዛት | በቁጥር | 13100 | 14412 | **11412** | 4412 | 3500 | 3500 | |
| | የተቀናጀ የአደገኛ ቆሻሻ እና የኬሚካል አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው መተግበራቸውን ክትትል እና ቁጥጥር የተደረገባቸው ተቋማት ብዛት | በቁጥር | 20 | 40 | **40** | 15 | 15 | 10 | |
| | የአካባቢ አያያዝ ክትትል እና ቁጥጥር የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች ብዛት | በቁጥር | 4359 | 5863 | **5063** | 1500 | 1600 | 1963 | |
| | የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ አቤቶታና ጥቆማ በመቀበል ማጣራትና ምላሽ መስጠት | በቁጥር | 2527 | 2696 | **2396** | 700 | 800 | 896 | |
| | የተለያዩ የዘርፍ ፕሮጀክቶች የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነዶቻቸውን በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ ወደ ትግበራ እንድገቡ ማድረግ፤ | በቁጥር | 7000 | 7300 | **5535** | 2000 | 2000 | 1535 | |
| | የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሳያካሂዱ ወደ ሥራ የገቡ ነባር ፕሮጀክቶችን የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እዲያቀርቡና እንዲያጸድቁ ማድረግ | በቁጥር | 1089 | 1520 | **770** | 200 | 300 | 270 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የይሁንታ ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች እና ፓርኮች የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት በማድረግ ክፍተት ባላቸው ፕሮጀክቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ | በቁጥር | 400 | 5117 | **3427** | 1200 | 1500 | 727 | |
| | በተጎዱ ሥርዓተ ምህዳሮች ላይ የተዘጋጀ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባ | በቁጥር | 4 | 4 | **4** | | 2 | 2 | |
| | በአካባቢ ዘርፍ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ብዛት | በቁጥር | 447 | 1150 | **150** | 50 | 50 | 50 | |
| | አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ የተወገደ አደገኛ ቆሻሻ | በቶን | 220 | 400 | **300** | 100 | 100 | 100 | |
| | የተዘጋጀ ዓመታዊ አካባቢ ህግ ተከባሪነት ዘገባ (ውሃ፣ አየር፣ ድምጽ፣ ማምረቻ፣ አበባ፣ ፕሮጀክት፣ ደረቅ ቆሻሻ እና ከሚካልና አደገኛ ቆሻሻ | በቁጥር | 6 | 8 | 8 | | | 8 | |
| | **ግብ 6፡- በአካባቢ ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ** | | | | | | | | |
| | የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የሚያመነጩትን ዋጋ ትመና የተካሄደባው ሥርዓተ ምህዳሮች | በቁጥር | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | | |
| | የቀነሰ መጤ ወራሪ አረም ሽፋን መጠን | በሚ/ሄ/ር | 0.162 | 0.16 | 0.125 | 0.04 | 0.04 | 0.045 | |
| | የደህንነተ ሕይወት ሥርዓት ተዘርግቶ የተቀነሰ ሊደርስ የሚችል ጠንቅ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | | | 1 | |
| | **ግብ 7- የመረጃና ቴክኖሌጂ አቅርቦትና ማሳደግ** | | | | | | | | |
| | የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም እና የልውውጥ ስርዓት ዕድገት | በመቶኛ | 20 | 30 | 30 | 26 | 28 | 30 | |
| | ስራ ላይ የዋለ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት | በቁጥር | 15 | 4 | **3** | 1 | 1 | 1 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የተሟላ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ተጠቃሚነት | | በመቶኛ | 53 | 60 | 60 | 56 | 58 | 60 | |
| | ተዘጋጅቶ የተሰራጨ አገራዊ ዘገባ/ሪፖርት | | በቁጥር | 4 | 6 | 6 | | | 6 | |
| | የተሸጋገሩ መረጃና ቴክኖሌጂ | | በቁጥር | 4 | 5 | 5 | | | 5 | |
| | **ግብ 8 ፡- የሴቶችና ወጣቶች ተሳትፎ ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | በዘርፎችና በክልሎች የሴቶች ተሳትፎ ስለመረጋገጡ ክትትል ማድረግ | | በቁጥር | 5 | 4 | **3** | 1 | 1 | 1 | |
| | በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት የበቁና ያደጉ ሴቶች ተሳትፎ ማሳደግ | | በመቶኛ | | 23 | **23** | 20 | 21 | 23 | |
| | **ግብ 9፡- የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ** | | | | | | | | | |
| | የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና | ወንድ | በቁጥር | | 1100 | 1400 | 800 | 600 | | |
| | | ሴት | በቁጥር | | 1100 | 700 | 400 | 300 | | |
| | የተሰጠ የረጅም ጊዜ ስልጠና በቁጥር | በመጀሪያ ድግሪ | በቁጥር | | 4 | 2 | | | 2 | |
| | | በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 10 | 6 | | | 6 | |
| | | በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | 4 | 4 | | | 4 | |

| ተ.ቁ | የአፈጻጸም አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2013 | የ2014 በጀት አመት ኢላማ | የ9 ወራት ዒላማ | የድርጊት መርሃ ግብር (የሩብ አመት ኢላማ) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | ምርመራ |
| | የተቀመረ ምርጥ ተሞክሮ ብዛት | በቁጥር | 2 | 7 | 4 | | | 4 | |